# በኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስቱ የህግ አወጣጥ ሥርዓት

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች:-**

ሰለሞን ወልደተንሳይ

ሰይፉ ገ/ማሪያም

በዚህ ጥናት ግኝት መሰረት አብዛኛዎቹ በፌደራል መንግስቱ የህግ አወጣጥ ስርዓት ውስጥ ያሉት ችግሮች የሚመነጩት የተቀመጠውን የአሰራር ስርዓት ካለመከተል የሚከሰቱናቸው፡፡ በመሆኑም መፍትሄ የሚሆነውም የአሰራር ስርዓቶቹን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ስርዓቱ የሚመራባቸው ደንቦችና መመሪያዎች በይዘታቸው ጥራት ያለው ህግ እንዲወጣ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ አሳታፊነትን እና በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረቱ ህጐችን ከማቅረብና ከማዉጣት ጋር በተያያዘ የሚኒስትሮች ምክርቤትም ሆነ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ደንብና መመሪያዎች በግልፅ ድንጋጌዎችን የያዙና የሚፈፀምበትን አግባብም የሚያሳዩ ሲሆን እየተከሰተ ያለው ችግር ግን ድንጋጌዎቹን ተከትሎ ካለመሄድ የሚመነጭ ነው፡፡

ረቂቅ አዋጆች ሲቀርቡ የሚያስፈልጋቸው ደንብ አብሮ ተያይዞ መቅረብ እንደሚኖርበትና በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በዓመታዊ የስራ እቅዱ እንዲወጡ የሚያስፈልጉትን አዋጅና ደንቦች ዘርዝሮ ማቅረብ እንደሚኖርበት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአሰራር መመሪያ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ይህን በተመለከተ እየተከሰተ ያለው ችግር ሊስተካከል የሚችለው በአሰራር መመሪያው የተቀመጠውን በመከተል ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩል ህጐችና አሰራሮችን በማውጣትና ተግባራዊ በማድረግ የህግ አወጣጥ ጥራቱን ለመደገፍ የሚቻልበት የመፍትሄ አቅጣጫም በቀላሉ ሊታይ የሚችል አይደለም፡፡ ወጥነትና ደረጃውን የጠበቀ የህግ አረቃቀቅን ለማስገኘት በተግባር ያሉ መልካም ልምዶችን ታሳቢ ያደረገና ያቀፈ የህግ ማርቀቅ ማንዋል መውጣት የማይተካ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በተመሳሳይም በህጐች መካከል ግጭቶችን መቀነስ እንጂ ማጥፋት የማይቻልና ዋስትና የሌለው በመሆኑ በህጐች መካከል ግጭቶች በሚኖርበት ጊዜ ተፈጻሚነትን በተመለከተ ወጥነት ባለው መልኩ የሚተገበር የአተረጓጐም ህግ እንዲወጣ ማድረግ አስፈላጊነት አለው፡፡

አዋጆችና ደንቦች በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትመው የሚወጡ ሲሆን በዚህ በኩል ያለውን የተደራሽነት

ውስንነት ትርጉም ባለው ደረጃ ማስተካከል የሚቻለው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድረ ገፅ አማካኝነት ወቅታዊነቱን በጠበቀ መልኩ አዋጆችና ደንቦች ተሟልተው እንዲካተቱ በማድረግ ነው። ይህም በአገሪቱም ሆነ በመላው የዓለም ክፍል በማንኛውም ጊዜ ሁሉ የፌደራሉ መንግስት አዋጆችና ደንቦችን በቀላሉ እንዲገኙ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ የሚያስከትለው የገንዘብ ወጪም አይኖርም።

መመሪያዎችን በተመለከተ ከአዋጆችና ከደንቦች በባሰ መልኩ የተደራሽነት ችግሩ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 ማናቸውም የመንግስት ተቋማት መመሪያዎቻቸውን በሚመለከተው ሰው ጥያቄ ባይቀርብም አስቀድመው ተደራሽ ማድረግ እንዳለባቸው እንዲሁም ደግሞ በሚጠየቁበት ጊዜ ተደራሽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ግዴታ ያስቀምጣል። ድንጋጌው ተግባራዊ ቢደረግና በተጨማሪም የአስተዳደር ስነስርዓት ህግ ቢኖር ይህንንና ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

በህግ ማርቀቅና በህግ አወጣጥ ሂደቱ ተሳታፊ የሆኑ የሚኒስቴር መስሪያቤቶችና የሚኒስትሮች ምክርቤት የህግ ጉዳዮች ቡድን ባለሙያዎች አቅምና አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ያለውን ክፍተት ለማስተካከል ከዚህ በላይ የተጠቀሱትም ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሙያዎቹን አቅም የሚያጐለብቱ የህግ ማርቀቅ ስልጠናዎች በየጊዜው እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል። በአደረጃጀት ደረጃ በየሚኒስቴር መስሪያቤቱ ያሉ የህግ ማርቀቅ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች አንዳንዶቹ ጋር ለሚኒስትሩ ተጠሪ ሆነው ራሳቸውን ችለው የሚደራጁ ሲሆን ሌሎች ጋር ደግሞ ተጠሪነታቸው ለሌላ የስራ ኃላፊ ሆኖ አደረጃጀታቸውም ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በአንድ ላይ የሚሆኑበት ሁኔታም አለ። ስለሆነም በየሚኒስቴር መስሪያቤቱ በተቻለ መጠን ወጥነት ባለው መልኩ የህግ ማርቀቅ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የሚደራጁበትና ተጠሪነታቸውም ለሚኒስትሮቹ የሚሆንበት አግባብ መፈጠር የሚኖርበት ሲሆን ይህም በተጨማሪነት ከመመሪያዎች ጋር በተያያዘ ያለው ተደራሽነትና በወቅቱ ያለመውጣት ችግርም ሚኒስትሮች በቅርበት እንዲከታተሉት ምቹ

ሁኔታን የሚፈጥር ይሆናል፡፡